


# የተከበሩ አቶ አያሌው ጎበዜ የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር

የአማራ ክልል ህዝብ በተለያዩ የመልክዓ ምድር እና የአየር ንብረት ውስጥ የሚኖር በመሆኑ የዘርፈ ብዙ ችግሮች ተጋላጭ ነው፡፡ ዛሬም የክልሉ ህዝብ በሰው ሰራሽና በተፈጥሮ አደጋ እየደረሰበት ያለውን ድቀትና ውስብስብ ችግር ለማስወገድ በተለያዩ መልኩ ታጥቆ ወደ ልማትና ሥልጣኔ እየገሰገሰ ይገኛል፡፡ ለዚህም ልማታዊ እንቅስቃሴው አጋዥ ከሆኑት ማህበራት ውስጥ አንዱ አማራ አቀፍ ልማት ማህበር (አልማ) ተጠቃሽ ነው፡፡

አማራ አቀፍ ልማት ማህበር (አልማ) ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ የክልሉ ህዝብ ያሉበትን የልማት ችግሮች በህዝብ፣ በመንግስትና በልማት ደጋፊ ሀይሎች የጋራ ጥረት እንጅ በተናጠል በሚካሄድ እንቅስቃሴ እንደማይፈታ አጥብቆ በማመን በክልሉ ውስጥ ዘላቂ የልማት ሥራዎችን ለመስራት ያመቸው ዘንድ የተለያዩ የገቢ ማሰባሰቢያ መድረኮችን በማዘጋጀትና በማመቻቸት ከአባላቶቹ፣ ከክልሉ ተወላጆችና የልማት ደጋፊዎች በሚሰባሰብ ገቢ አማካኝነት፣ በክልሉ ውስጥ በትምህርትና በጤናው መስክ፣ በመልሶ ማቋቋም፣ በመንገድ ግንባታ፣ በተፈጥሮ ሃብት ልማትና ጥበቃ፣ በገጠር ሴቶችና በቀድሞ ወታደሮች ዙሪያ፣ ከኤች አይ ቪ ኤድስ ቫይረስ ጋር አብረው ለሚኖሩ ሰዎች፣ ለአካል ጉዳተኞች፣ በዝቅተኛ ደረጃ የሚኖሩ ሴቶች እና ወጣቶችን በሚያግዝ መልኩ የተለያዩ እንቅስቃሴዎች ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

አልማ ህብረተሰቡን በማሳተፍ ከልዩ ልዩ ምንጮች የሚያገኘውን ሃብት በማሰባሰብ የህዝቡን የልማት ጥረት የመደገፍ ተልዕኮውን መሰረት በማድረግ ካለፉት 3 ዓመታት ወዲህ አዲስ የአሰራር ስልት በመቀየስ ከእያንዳንዱ ወረዳ አባላትና ደጋፊዎች ከሚሰበሰበው ገንዘብ 70 በመቶው በወረዳው አልማ አማካኝነት በየወረዳው ለሚከናወኑ የትምህርትና የጤና ፕሮጀክቶች፣ 30 በመቶው ደግሞ ወደ ዋናው ጽ/ቤት ተሰባስቦ በክልሉ ለታቀዱ ተግባራት ማስፈጸሚያነት በማዋል በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት መስኮች አያሌ መልካም ውጤቶችን በማስመዝገብ ላይ ይገኛል፡፡

ማህበሩ “የአማራ ክልል ችግሮች እጅግ የከፉና የተወሳሰቡ ቢሆንም፤ ሁሉም የልማት ወዳድ ወገኖች እንደ ወትሮው ሁሉ ተባብረውና ተደጋግፈው ከሰሩ ችግሮች መፈታት ይችላሉ” ብሎ በማመን አሁንም “አልማ 2002 ልማታዊ ህብረት” በሚል የልማት ጥሪ አማካኝነት በክልሉ ውስጥ የተለያዩ ተግባራትን ለማከናወን አቅዶ ተነስቷል፡፡ በመሆኑም የማህበሩን ጥሪ ተቀብላችሁ ድጋፍ ላደረጋችሁ በሙሉ በክልሉ ሕዝብ፤ በክልሉ አስተዳደርና በራሴም ስም ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ ወደፊትም አልማን በመደገፍም ሆነ በኢንቨስትመንትና በልዩ ልዩ መልኮች ከጎናችን ሆናችሁ እንደምትቀጥሉ ሙሉ ተስፋና እምነት ያለኝ መሆኑን እገልፅላችኋለሁ፡፡

አመሰግናለሁ



# አቶ ህላዌ ዮሴፍ የአልማ ሥራ አስፈፃሚ ቦርድ ሊቀመንበር

አማራ አቀፍ ልማት ማህበርን (አልማ) መመስረት አስፈላጊ ሆኖ በተገኘበት ወቅት በአማራ ክልልም ሆነ በአጠቃላይ በአገራችን የነበረው ማህበረ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ እጅግ አስከፊና አሳዛኝ ነበር፡፡

በ1985 ዓ.ም. እንደ አንድ ክልል በተደራጀው በአማራ ብሔራዊ ክልል የታቀፉት የቀድሞዎቹ የሰሜንና ደቡብ ጎንደር፣ ሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ ምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፣ እንዲሁም ሰሜን ሸዋ ክፍላተ ሀገራት በአገራችን የተካሄደው ጦርነት ክፉኛ የጎዳቸው አካባቢዎች ናቸው፡፡ በተለይም የወሎና የጎንደር አካባቢዎች አብዛኛዎቹ ወረዳዎች ከ1960ዎቹ መጨረሻ ጀምሮ የጦርነት እሳት ሲለበልባቸው መኖሩ ይታወቃል፡፡ ከቀድሞውም እጅግ ኋላ ቀር በነበረው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታ ላይ የጦርነቱ መጨመር መላው የክልሉን ሕዝብ ለከፋ ህሊናዊ ሰቆቃና ለድህነት መዳረጉ ነበር የአልማን ምሥረታ የወቅቱ ትልቅ አጀንዳ ያደረገው፡፡

እናም አልማ ግንቦት 20 ቀን 1984 ዓ.ም. ተመሠረተ፡፡ እንደተመሰረተም "እጅግ የተወሳሰቡትና ሥር የሰደዱት የአማራ ሕዝብና ክልል የልማት ችግሮች በሕዝብ፣ በመንግስትና በልማት ደጋፍ ኃይሎች የጋራ ጥረት እንዲ

## መልዕክት


በተናጠል ሊፈቱ አይችሉም፣ ለዚህም በራስ መተማመን ላይ በተመሠረተ ዓላማና በክልል አቀፍ ማህበር ዙሪያ ለአማራ ልማት አስተዋፅኦ እናድርግ" የሚል ጥሪ አሰማ፡፡ "በዚህ ዓላማ ዙሪያ ለመሰባሰብም የሃይማኖት፣ የፖለቲካ አስተሳሰብና የሃብት ደረጃዎች መለያያ ጉዳዮች ሊሆኑ አይገባም" የሚል እምነትን የማዕዘን ድንጋዩ አደረገ፡፡

ይህን የአልማ የልማት አስተሳሰብና የማዕዘን ድንጋይ የራሳቸው አድርገው በአማራ ክልልና በሌሎች የአገራችን ክልሎች የሚገኙ ልማት ወዳድ ባለሃብቶች፣ አገር አቀፍና አለም አቀፍ ግብረ-ሰናይ ድርጅቶች፣ በክልላችን የሚገኙ እህት የልማት ድርጅቶች፣ሲቪል ሰርቫንቶች፣ በማንኛውም ወቅት ለማንኛውም የሰናይ ተግባር ጥሪ ወደ ኋላ ብለው የማያውቁት የመከላከያና የፖሊስ ሃይሎች፣ በውጪ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን፣ አርሶ አደሮችና ላብ አደሮች፣ የስነጥበብና የመገናኛ ብዙሃን ሙያተኞች፣ ምሁራን፣ ተማሪዎችና ወጣቶች ከጎኑ ተሰልፈው ትልቅ የልማት ሠራዊት ሆነዋል፡፡ ለእነዚህ ሁሉ ወገኖች ምስጋን ይግባቸውና ከእነሱ ባስተባበረው ጉልበት፣ እውቀት፣ ገንዘብና ቁሳቁስ ባለፉት 18 ዓመታት እንደ ሃውልት ገዝፈው የሚኖሩ አኩሪ የልማት ተግባራትን አከናውኗል፡፡

በአልማም ሆነ በክልሉ መንግሥትና ሕዝብ እንዲሁም በሌሎች የልማት አጋሮች በተደረገው ርብርብ በሁሉም መስኮች አበረታች ውጤቶች ቢመዘገቡም፣ አሁንም መፈታት ያለባቸው በርካታ የልማት ችግሮች አሉ፡፡ ዛሬም በፈረሱ ት/ቤቶችና በዛፍ ጥላ ስር የሚማሩትም ሆነ የትምህርት ዕድል ያላገኙት ህፃናት ቁጥር እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡ የጤና አገልግሎት በበቂ ሁኔታ ያልተዳረሰባቸው አካባቢዎችም አሉ፡፡ ሥራ አጥነትን ለመቀነስ ወጣቶችን ማሰልጠንና ራሳቸውን የቻሉ ብቁ ዜጎች እንዲሆኑ የሚያስችል ሁለገብ ድጋፍ መስጠት አሁንም ከፊታችን የተደቀነ ትልቅ የቤት ሥራችን ነው፡፡

አልማ የአማራ ክልል ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች እንዲቃለሉ ባለፉት 18 ዓመታት የልማት ቀዳሚ ዘማች ሆኖ እንደተረባረበው ሁሉ፣ አሁንም በዚሁ ጥረቱ ተጠናክሮ ለመቀጠል ከመቼውም ጊዜ በላይ ራሱን አዘጋጅቷል፡፡ "አልማ 2002 ልማታዊ ሕብረት" የተሰኘውና ነባሩን የልማት ኃይሎች ትብብር ይበልጥ የሚያጠናክር የልማት ሃብት የማሰባሰብ እንቅስቃሴም የዚህ ዝግጅት አካል ነው፡፡

የአልማ 2002 ልማታዊ ሕብረት የገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራማችን ዋነኛ አላማ ተደጋግፈን ከፊታችን የተደቀኑትን ችግሮች እንድናቃልላቸው ማስቻል ነው፡፡ አልማ ከአሁን ቀደም በድጋፋቸው ሳበረቱትም ሆነ ለዚህ ታላቅ የገቢ ማሰባሰቢያ እቅድ መሳካትም የተለመደውን ትብብራቸውን ሳደረጉለት ሁሉ በልማቱ ተጠቃሚ ሕዝብ ስም ምስጋናውን ያቀርባል፡፡





# አቶ ሰለሞን ታደሰ የአልማ ዋና ዳይሬክተር

ማህበራችን አልማ በታሪኩ ልዩ ምዕራፍ ላይ ደገኛል። ከመቼውም ጊዜ በላቀ ሁኔታ የክልሉን ህዝብ ልማታዊ ህብረት በማጠናከር ባለፉት 18 ዓመታት ያከናወንናቸውን የልማት ተግባራት በእጥፍ ለመፈጸም የሚያስችለውን ታላቅ የገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራም "አልማ 2002፡ ልማታዊ ሕብረት" በሚል መሪ ቃል ስር ሲያከናውን ቆይቷል።

የልማታዊ ህብረቱ መሠረታዊ ዓላማ የክልሉን ህዝብ የልማት ችግሮች በማስገድ በመንግስት፣ በግሉ ክፍለ ኢኮኖሚና በህዝቡ የሚደረገውን ያለውን ርብርብ ትርጉም ባለው ደረጃ ለማገዝ የሚያስችለንን ህዝባዊ የልማት አንድነት ማጠናከር ነው። በሚፈጠረው ህብረትና ከእያንዳንዳችን በሚበረከት የሙያ፣ የገንዘብ እና የጉልበት አስተዋፅኦም በትምህርት፣ በጤና በስፖርት እና በሙያ ስልጠና ረገድ ያሉብንን ክፍተቶች ለመሙላት የሚያስችል ትልቅ አቅም እንፈጥራለን።

የልማታዊ ህብረቱ በደፋ ታውጆ እንቅስቃሴ ከጀመርንበት ጊዜ ጀምሮ በህዝቡ ዘንድ የታየው የጋለ ንቅናቄ ለክልሉ ህዝብ በአጠቃላይ አኩሪ ሆኗል። እጅግ በጣም በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ያሉ ከዕለት ጉርሳቸው በመቀነስ ድጋፍ አድርገዋል። ጡረተኞች ያላቸውን አነስተኛ የጡረታ ገንዘብ አሚጠው በመስጠት የአካባቢያቸው የልማት ችግር መፍትሄ አግኝቶ ለማየት ያላቸውን ጉጉት አሳይተዋል። የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች "በተጎሳቆሉና ምቹ ባልሆኑ ት/ቤቶች መማር በእኛ ይብቃ" ሲሉ ከዕለት የምግብ ራሽናቸው በመቀነስ ድጋፍ አድርገዋል። የመንግስት ሠራተኞች ከወር ገቢያቸው ከ10% እስከ የአንድ ወር ደሞዛቸውን ለመስጠት ቃል ገብተዋል። በቃላቸውም መሠረት ድጋፋቸው በመሰብሰብ ላይ ደገኛል። ባለሃብቶችም በመቶ ሺዎችና በሚሊዮኖች የሚያወጡ የትምህርትና የጤና ፕሮጀክቶችን ሙሉ ወጪ በመሸፈን ሰርቶ ለማስረከብ ቃል ገብተዋል።

በአጠቃላይ የተፈጠረው ህዝባዊ ንቅናቄና ለክልላችን ልማት ሁሉም ወገን ያሳየው ቀናዒነት እጅግ የሚያኮራና ካለንበት የድህነት አረንቋ በአጭር ጊዜ ለመውጣት የሚያስችል የብሩህ ተስፋ ብርሃን ፈንጥቆልናል።

ማህበራችን የጀመራቸው ታላላቅ ውጥኖች ከዳር ሊደርሱ የሚችሉት ግን አሁን የተፈጠረው ህዝባዊ የልማት አንድነትና ርብርብ በአስተማማኝ መሠረት ላይ ሊጣልና ቀጣይነት ሲኖረው ብቻ ነው። ለዚህም ሚሊዮኖች አንድ ሆነን በዚህ ልማታዊ ህብረት ጉልህ ተሳትፎ እንዳደረግን ሁሉ፣ የማህበሩ አባል በመሆን ድህነትን ተረት አድርገን ለማስቀረት አልማ በሚያደርገው ትግል ውስጥ የበኩላችንን ድርሻ እንድንወጣ ይጠበቅብናል። ሚሊዮኖች አባል ሆነው የድጋፍ እጃቸውን ከመዘርጋት ባሻገር በቅርብ ሆነው እንደባለቤት ሊከታተሉትና ሊጠይቁት ይገባል።

በመጨረሻም ይህ የተፈጠረው መልካምና ታሪካዊ መነሳሳት ፍሬ አፍርቶ ማየት እንድንችል በየትኛውም ቦታ የምንኖር የክልሉ ተወላጆችም ሆንን የልማቱ ደጋፊዎች ልማታዊ ህብረታችንን አጠናክረን እንድንቀጥል በታላቅ አክብሮት እጠይቃለሁ።